የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፹፩
አዲስ አበባ ነሐሴ ፯ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No. 81
ADDIS ABABA 13th August, 2019

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፶፯/፪ሺ፲፩ ዓ.ም

የተጨማሪ እሴት ታክስ (ማሻሻያ)አዋጅ....ገጽ....፲፩ሺ፭፻፴፬

Content

Proclamation No. 1157/2019

Value Added Tax (amendment)Proclamation..Page 11534

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፶፯/፪ሺ፲፩

## የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፭/፲፱፻፺፬ (እንደተሻሻለ) እንደገና ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የተጨማሪ እሴት ታክስ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፶፯/፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ማሻሻያ

የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፭/፲፱፻፺፬ (እንደተሻሻለ) ከዚህ እንደሚከተለው እንደገና ተሻሽሏል፡-

፩ የአዋጁ አንቀጽ ፪ (፩) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል፡፡

Proclamation No.1157/2019

## A PROCLAMATION TO AMEND THE VALUE ADDED TAX

WHEREAS, it has become necessary to further amend the Value Added Tax Proclamation No.285 /2002 (as amended);

NOW, THEREFORE, in accordance with article 55 (1) and (11) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows.

1. Short Title

This proclamation may be cited as the "Value Added Tax (amendment) Proclamation No.1157/2019."

2. Amendment

The Value Added Tax Proclamation No.285/2002 (as amended) is hereby further amended as follows:

1/ Article 2 (1) is deleted and replaced by the following new sub-article (1).

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 4.90

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

"፩/ "የሂሳብ ጊዜ" ማለት:-

ሀ) በማናቸውም የ፲፪ ወራት ጊዜ ውስጥ ያከናወነው ጠቅላላ ሽያጭ ብር ፸ ሚሊዮን (ብር ሰባ ሚሊዮን) እና ከዚህ በላይ ለሆነ ታክስ ከፋይ እያንዳንዱ ወር፣

ለ) በማናቸውም የ፲፪ ወራት ጊዜ ውስጥ ያከናወነው ጠቅላላ ሽያጭ ከብር ፸ ሚሊዮን (ከብር ሰባ ሚሊዮን) በታች የሆነ ታክስ ከፋይ ፫ ወር ሲሆን፤ የነሐሴና የጳጉሜ ወራት እንደአንድ ወር ይቆጠራሉ።"

፪/ የአዋጁ አንቀጽ ፪ (፬) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተተክቷል።

"፬. "ባለስልጣን" ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር ነው።"

፫/ ከአዋጁ አንቀጽ ፪ (፳፮) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፳፯) ተጨምሯል።

"፳፯/ "የካፒታል ዕቃ" ማለት ለሽያጭ የሚውሉ ምርቶችን ለማምረት ወይም አገልግሎቶችን ለመስጠት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ጥቅም ላይ የሚውል ከአንድ ዓመት በላይ አገልግሎት ሊሰጥ የሚችል ንብረት ሲሆን፤ ህንፃን፣ ተሽከርካሪን፣ መሣሪያን እና እነዚህን የመሳሰሉ ግዙፋዊ ህልውና ያላቸውን ሌሎች ንብረቶች ይጨምራል።"

፬/ የአዋጁ አንቀጽ ፯ (፭) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተተክቷል።

"፭. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ (ሀ) ተፈፃሚ የሚሆንበት ግብይት ሲከናወን:-

ሀ) የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰነው መሠረት ታክሱ ግዥውን በሚፈጽመው አካል ተይዞ ለባለሥልጣኑ ይከፈላል።



"1/ "Accounting period" shall means:

a) In the case of taxpayers whose turnover in any 12 months is birr 70,000,000 (birr seventy million) and over, every month;

b) In the case of taxpayers whose turnover in any 12 months is less than birr 70,000,000 (birr seventy million) every three months, wherein the month of Nehasse and Pagumen shall be aggregated and treated as one calendar month."

2/ article 2 (4) is deleted and replaced by the following new sub-article (4).

"4. "authority" means the Ministry of Revenue."

3/ new sub-article (27) is added following article 2 (26) of the Proclamation.

"27/ "capital good " means an asset with a life time of more than one year, used directly or indirectly in the manufacture of goods and in the rendition of services and includes building, vehicle, machinery, equipment, and other similar tangible assets ."

4/ article 7(5) is deleted and replaced by the following new sub-article (5):

"5/ in the case of transactions to which sub-article 1 (a) of this article is applicable.

a) the tax shall be withheld and paid to the authority by the buyer in accordance with the directive to be issued by the Minister of Finance;

ለ) በዚህ አንቀጽ መሠረት በገዥው ተይዞ የሚከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ተከፋይ የሆነው ታክስ ፶ ፐርሰንት ሲሆን ቀሪው ለሻጩ ይከፈላል፡፡"

፭/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፩ (፮) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፮) ተተክቷል፡፡

"፮/ ሀ) ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ወይም መመዝገብ ያለበት ሰው ከመመዝገቡ በፊት ባሉት ፮ ወራት ጊዜ ውስጥ ለገዛቸውና በይዞታው ሥር ለሚገኙ ዕቃዎች የከፈለው ታክስ፣ ዕቃዎቹ ታክስ ለሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የዋሉ ወይም የሚውሉ መሆኑ ከተረጋገጠ፣ ታክስ ከፋዩ በተመዘገበበት ወይም መመዝገብ በነበረበት የመጀመሪያ የሂሣብ ጊዜ ሊከፍል ከሚገባው ታክስ ላይ ተቀናሽ ይደረጋል፡፡

ለ) በማናቸውም የ፲፪ ወራት ጊዜ ውስጥ ያከናወነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ከብር ፩፻ ሚሊዮን (ከብር አንድ መቶ ሚሊዮን) በላይ የሆነ ታክስ ከፋይ በተመዘገበበት ጊዜ በእጁ የሚገኙ ወይም ከተመዘገበበት ጊዜ በኋላ ባለው የሂሣብ ጊዜ የገዛቸው የካፒታል ዕቃዎች ታክስ ለሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የሚውሉ መሆኑ ከተረጋገጠ በካፒታል ዕቃዎቹ ላይ የተከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ በሚቀጥለው የሂሣብ ጊዜ ሊከፍል ከሚገባው ታክስ ላይ ተቀናሽ ይደረጋል፡፡"

፮/ ከአዋጁ አንቀጽ ፳፯ (፮) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (፯) እና (፰) ተጨምረዋል፡፡

"፯/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፩ (፮) (ለ) የተደነገገው ቢኖርም በካፒታል ዕቃ ላይ የተከፈለ ታክስ በሚቀጥለው የሂሣብ ጊዜ እንዲቀናነስ ከተደረገ በኋላ ቀሪ ሂሣብ ቢኖር ባለሥልጣኑ ይህንን ቀሪ ሂሣብ ከሂሣብ ጊዜው ቀጥሎ ባለው የአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለታክስ ከፋዩ ተመላሽ ማድረግ አለበት፡፡

b) the tax withheld in accordance with this article shall be 50 percent of the tax payable by the buyer and the balance shall be paid to the seller.

5/ Article 21 (6) is deleted and replaced by the following new sub-article (6).

"6/ a) a person who registers or has to register for vat shall be entitled to credit under this article in the first accounting period in which the person is registered or has to register for vat, on the amount paid on goods at hand on the date of registration and that are used or to be used for the taxable transaction, but only to the extent that the purchase or import of the goods occurred not more than six months before the date of registration.

b) a person whose 12 months taxable transaction exceeds birr 100,000,000 (birr One hundred million) shall be entitled to credit under this article in the accounting period after the date of registration on the amount of value added tax paid on capital goods at hand or purchased after the date of registration that is used or to be used for taxable transaction .

6/ the following new sub-articles (7) and (3) are added following article 27 (6).

"7/ notwithstanding the provision of article 21 (6) (b) of this proclamation, the authority shall refund the remaining amount of vat paid on capital goods in excess of the amount credited in the accounting period within the coming one month.

፰/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚከፈለው የታክስ ተመላሽ የሚመራበት የሥጋት ሥራ አመራር መርህን የተከተለ የተመላሽ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት።"

፫. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ነሐሴ ፯ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

ሣህለወርቅ ዘውዴ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚደንት

8/ the authority shall implement risk based refund system for refund to be paid in accordance with this article."

3. <u>Effective Date</u>

This proclamation shall enter into force on the date of its publication on the negarit gazette.

Done at addis ababa this 13th day of August, 2019

SAHLEWORK ZEWDIE

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት